# የ AFD መዘዝ : ቀስ በቀስ ሲመዘዝ

ሰሞኑን በኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የሚመራው ቅንጅት ጥገኝነትን አመልክቶ ስለመከልከል የሚገልጽ ጽሑፍ በየ ድኅረ ግጾች ላይ አውጥቶ ተመልክቻለሁ ጉዳዩ በቀጥታ እነማንን በተመለከተ እንደሆነ ባያብራራም በደፈናው በራሴ ግምት (ግምቴም እምብዛም የተሳሳተ አይምስለኝም በቅርቡ ከሐገር ቤት ስለመጡት ግለስቦች የሚዘግብ ይመስለኛል) ሆኖም ግን ተሳስተሀል ከተባልኩ ሂሴን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ::

ይህን ካልኩ በኋላ ወደ ዋናው የተነሳሁበት ቁም ነገር ልመለስና ከላይ በጠቀስኩት እነ ኢንጂነር ኃይሉ አካባቢ ያሉና በቅርቡ ከሐገር ቤት ከመጡ ግለስቦች መሀከል ለአንዱ ወይንም ከዚያም በላይ ሊሆኑ ለሚችሉ ግለሰቦች እዚህ አሜሪካ ሐገር ውስጥ በጥገኝነት ለመኖር የሚያስችል የፍቃድ ወረቀት እንዲሰጣቸው እንዳመለከቱ ከጽሁፉ መገንዘብ ችያለሁ : በአንጻሩም (U.S. Department of Homeland Security) ጉዳያቸውን ተመልክቶ እኛ ቀደም ሲል ተዉ የ AFD ጉዳይ አያዋጣም አይሆንም በዚህም ሁኔታ ላይ መግለጫ በማውጣት አቋማችሁን ግልጽ አድርጋችሁ አውግዛችሁ ልትወጡ ይገባል እያልን ስንጮህበት በነበረው ይኸው መዘዘኛ AFD በመባል የሚታወቀው ጸረ ኢትዮጵያ የሆነን ስብስብ አካልና ተባባሪ ናችሁ በማለት እንደዋና የመከልከያ ምክንያት በማድረግ የጥገኝነቱን ማመልከቻ እንዳልፈቀደላቸው የሚገልጽ ጽሁፍ አውጥተዋል:: እነሱም የተከለከሉበት ጉዳይ አለአግባብ እንደሆነና ኢንጂነር ኃይሉ ከዚህ ቀደም ዋሽንግተን ዲሲ በተደረገ ስብሰባ ወደ 800 የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን በተሰበሰቡበት ስለ AFD ተጠይቀው ሲመልሱ CUD ከማንኛውም በሰላማዊ ትግል ከሚያምን ጋር ተባብሮ ለመስራት ፈቃደኛ መሆናቸውን እና ከዚህ ከሚባለው ድርጅት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የለንም በማለት ተናግረዋል ሲሉ የዋሽንግተኑን ስብሰባ ዋቢ በማድረግ በማመልከቻቸው ላይ የተሰጠው ብያኔም አግባብነት እንደሌለው ይኸው ከላይ የተጠቀሰውን መስሪያ ቤት በበላይነት የሚመሩትን (F. Gerard Heinauer) የሚባሉ ግለሰብ ውሳኔያቸውን እንደገና እንዲመረምሩላቸው ይማጸናል::

ቁም ነገሩ ቀድሞውንም ይህንን መዘዘኛ የሆነ በሻቢያ ግምባር ቀደም አቀንቃኝነት የተመሰረተ AFD የሚባል ዝባዝንኬያም የፖለቲካው ሀሁ በውል ባልገባቸው ግለሰቦችና በመሰሪ የወያኔ ጉዳይ አስፈጻሚ በሆኑ የበግ ለምድ የለበሱ አጃቢ ነበርን ባዮች አሳዊ መሲሆች አራጋቢነት ተፈርሞ ለዛሬው ትርኢት አብቅቶናል:: ይህም ብቻ ሳይሆን በኢንጂነር ኃይሉ ወገን ይህ ጸረ ኢትዮጵያ የሆነ AFD የሚባል ሰነድ በእውነትም ጸረ ኢትዮጵያ አቋም እንዳለው ከተገነዘቡ ምንም እንኳ እኛ በታሰርንበት ጊዜ ስለሰነዱ ተብታቢነት በውል ያልገባቸው ግለስቦች የፈረሙት ነው እኛ አንቀበለውም ብሎ እንደ ቀላል ነገር ከመግፋት ይልቅ አግባብ ያለው መልስ በመስጠት ለ AFD ግባተ መሬቱን ማወጅ ቀዳሚና አስፈላጊ ጉዳይ ነበር ::

የወከሏቸው ግለሰቦች በድርጅቱ ስም የተፈራረሙት ሕጋዊ ሰነድ መሆኑን አምነው ስነ ስርአቱን በተከተለ መልኩ AFDን የሚያወግዝ ጽሑፍና አስፈላጊም ከሆነ ተፈራርመው እንደተወዳጁ ሁሉ ተፈራርመው ወዳጅነታቸውን ማፍረስ ይገባቸው እንደነበር እንዴት ሚስጢር እንደሆነባቸው አሁንም ሊገባኝ አልቻለም:: በየመድረኩና በየስብሰባው በሰላማዊ ትግል ከሚያምኑ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ጋር ለመስራት ዝግጁ ነን ማለቱ ብቻ በቂ አይደለም ነገሩን አስረግጦ ለማለፍ AFDን በስም ጠርቶ ማውገዝና በዚሁ ጸረ ኢትዮጵያ በሆነ ስብስብ ላይ አስፈላጊውን እርምጃ በማያሻማና

በማያዳግም ሁኔታ ማቅረቡ ከቁርጠኛ ኢትዮጵያዊ ታጋይ የሚጠበቅ እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ነው :: እንዲያው ሾላ በድፍኑ ነገሮችን በሰምና ወርቅ እያሰቀመጡ እንዲህ ሲሉ እንዲህ ማለታቸው ነው የሚባለው ትርጓሜ ሊሰጠው የሚያስችል አመላለስ መልስ መስጠቱ ነገሮችን ይበልጥ ውስብስብ እንዲሆኑ ከማድረግ በላይ በራሱ ለገጠመን ችግር አጥጋቢ መፍትሄ ሊሆን እንዳልቻለ እየታየ ነው:: እንደመሰረቱት ሕብረት ተብዬው ለማፍረስም ሆነ ተቀባይነት እንደሌለው ለማስቀመጥ ግልጽነትና ቁልጭ ባለ ሁኔታ ስላልተሄደ "ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ" እየተሆነ ይኸው አሁን ለተደረሰበት መሰናክል አብቅቷቸዋል በየጊዜው የሚሰጡት መልስና አቀራረብ የሚያሻማ መስሎ ስለሚታይና ስለሆነም ከተዘፈቁበት ማጥ ቀላል የማምለጫ መፍትሄ ሊሆን አልቻለም ::

እስከ አሁንም ድረስ AFDን በሚመለከት የሚሰጠው መልስ ለምን በጥቁርና ነጭ ማስቀመጡን እንደተቸገሩ ለኔ በጣም ግራ አጋብቶኛል :: እኛ አልፈረምነውምና አስፈላጊ አይደለም ወይም እኛን አያገባንም ማለቱ እራስን ከማታለል በቀር መፍትሄ አይሆንም ሊሆንም አይችልም : እንዳልሆነም በተግባር ውጤቱን እያሳየ ነው :: አንድ ግለሰብ የድርጅት ባለቤት ሆኖ ሳለ ለጊዜው ድርጅቱን ባንዳንድ ሁኔታዎች ሊመራ ባይችልና ድርጅቱን እንዲመራለት አንድ ሰው ወይንም የተወሰኑ ግለሰቦችን በሱ ሥም ስለሱ ሆነው እንዲሰሩለት ውክልና ሰጥቶ የተወከለው ግለሰብ የሚሰራቸው ስራዎች የሚፈራረማቸው ፊርማዎችና የሚያከናውናቸው ማናቸውም ተግባራት ሁሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በውክልና የተቀመጠው ግለሰብ ሥራ ብቻ ሳይሆን የድርጅቱ ባለቤትም ሥራ እንደሆነ መገንዘብና ማወቅ ከዚያም ባሻገር በህግ አኳያም እንኳ ቢሆን ሊያፋናፍን የማያስችል ሰንካላ ምክንያት መሆኑን ለመረዳት አለመቻላቸው: ሊያመጣ የሚችለውንም አደጋ አስቀድሞ ማየት ጭምር እንዴት እንደተሳናቸው ሳስበው ነገሮችን በቀላሉ የመገንዘብ ችሎታና ብቃታቸው እምን ድረስ እንደሆነ ለመገመት ያዳግተኛል::

እኛ በሌለንበት የተፈረመ ነውና እኛን አያገባንም ብሎ እንደ ጲላጦስ እጅን ታጥቦ መሄዱ አንድ አያዋጣም: ሁለትም በሕዝብ ዘንድ በከፍተኛ መስዋዕትነት የተገኘን አመኔታን ይሸረሽራል ስለሆነም አሁን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እያመዘነ መምጣቱን ሳይወዱ በግድ መቀበል የግድ ይላል :: ለሚሰሩትም ስራ እንቅፋት ሆኗል ለውደፊትም በጊዜው ካልታረመ በብዙ መልኩ እንቅፋት መሆኑ አይቀሬ ነው:: ከዚህ ቀደም እኛ ማለት ብዙሃኑ እትዮጵያውያን አስቀድመን ስንናገር የነበረውን ሁሉ እውነትነቱን ተቀብሎ አላማን ማስተካከሉ አይቀሬነቱን ቁልጭ አድርጎ እያሳያቸው ነው:: በሌላው ወገን ብንመለከት ደግሞ እኛ በሌለንበት የተፈረመው አያገባንም ማለቱ ወንዝ ካለማሻገሩም በላይ "ሲሞቅ በማንኪያ ሲቀዘቅዝ በእጅ" የሚያሰኝ ተግባር ከመፈጸም ያልተናነሰ ድርጊት ነው ::ይህንን በታኝ የሆነ ሰነድ የፈረሙትና በታዛቢነት አጅበን ነበር የሚሉት ግለሰቦች አልነበሩም እንዴ በቅንጅት ስም የሚያደራጁት : በቅንጅት ስም አልነበረም እንዴ ገንዘብ የሚያሰባስቡት: የአሜሪካንንም ሆነ የአውሮፓን መንግስታት የሚያነጋግሩት: በቅንጅት ስም አልነበረም እስረኞችንም ለማስፈታትም ሆነ ኢትዮጵያዊውንም ለማደራጀት ይባስ ብሎም ለመበተን የሚንቀሳቀሱት የነበረው? ታዲያ በቅንጅት ሥም የሰሩትን ጥሩ ጥሩ ነገር ተቀብሎ ላብዛኛው ኢትዮጵያዊ አልዋጥልህ ያለው ጉዳይ ላይ ሲደረስ እኛ በሌለንበት በኛ ሥም የተፈረመ ነውና አያገባንም ማለቱ እውን ቅንጅትን ለማጥፋት ቀን ከሌት ደፋ ቀና ለሚለው ለወያኔም ጭምር ተከራክረው ሊረቱት የማይችሉት እራስን የማጥፊያ ጥይት ማቀበል አይሆንም? እንዴት አንድ አገርን ለመምራት ታላቅ አመኔታ የተጣለበት ትልቅ ድርጅት ይሄንን

ለማንም ያልተሰወረ ገሃድ የሆነ ጉዳይ ከነሱ ሊሰወር ቻለ? መልሱን ለአንባቢያንና ለቅንጅት የበላይ አመራሮች እተወዋለሁ::

አሁንም በዚህ ጉዳይ ላይ እርምት ለመውሰድ በቂ ጊዜ አላቸው ብዬም አምናለሁ : "ከቀረ የዘገየ ይሻላልና": ለወደፊቱም ከንደዚህ አይነቱ ዝባዝንኬ እየተነከርን ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ እንዳይሆን አሁንም በዚህና መሰል ጉዳዮች ላይ አቋምን በማያሻማ ማስቀመጡ ይጠቅማል እንጂ ጉዳት ያለው አይመስለኝም ፖለቲካን በሰምና ወርቅ እያስቀመጡ እንቆቅልሹን ፍቱ ማለቱ ለጊዜው ከተወረወረ ጊዜያዊ ፍላጻ ያዳነ ቢመስልም ወሎ አድሮ ግን እንቆቅልሹም ሳይፈታ ይባስ ብሎ እራሳችን የተናገርነው እንቆቅልሽ ለራሳችንም እንቆቅልሽ መሆኑ አይቀሬ ነውና ይታሰብበት እላለሁ::

ከ ሰውነት ዳኜ : ሰሜን አሜሪካ

ድል ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ !!